
# ዜና መጽሄት

ፕሮጀክት SMILE - የ ERP ትግበራ በየወሩ የሚታተም

ጥቅምት , 2016

# የፕሮጀክቱ ተልዕኮ

የኢትዮጵያ የመድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት በ2030 በአፍሪካ እጅግ ፈጣን ምላሽ ሰጪ እና ቀልጣፋ የመድኃኒት አቅርቦት ሰንሰለት እንዲኖረው የያዘውን ራዕይ ዕውን እንዲያደርግ ወሳኝ ሚና መጫወት ነው።




ለተጨማሪ መረጃ

የፕሮጀክቱን ዌብሳይት ይጎብኙ

https://erp-portal.epss.gov.et/

# የውስጥ ገጾች ዜና መጽሄት

ፕሮጀክት SMILE - የ ERP ትግበራ በየወሩ የሚታተም

ጥቅምት, 2016


**01**

[redacted]

**አጠቃላይ እይታ**

**02-05**

[redacted]

**ዜና**

**06**

[redacted]

**አሁናዊ**

**07**

[redacted]

**ቀጣይ**

**08**

[redacted]

**ቲፕ**


SMILE Monthly is a change management product for the SAP-S4/HANA ERP implementation. For Comments and feedback please write to the internal change management teams.

https://erp-portal.epss.gov.et/speakup.php

SAP S/4 HANA


**Prepared by: - Adina Berie**

**Reviewed by: - Kaleab Sileshi**

**Approved by:- EPSS PMO Team**

# አጠቃላይ እይታ

1

**ማቀላጠፍ** – የተቋሙን የስራ ፍሰት በማቀላጠፍና በቴክኖሎጅ በማገዝ የመረጃዎችን ትክክለኛነትን በማሻሻል ጊዜን እና ገንዘብን መቆጠብ ያስችላል

**መለካት**– ሁሉንም መረጃዎች በማዋሃድ እና በቀላሉ በመተንተን የተቋሙን የዕለት ተዕለት ስራዎችን እንዲለካ ያግዛል።

**ፈጠራ** –፡- የተቋሙ አመራሮችና ሰራተኞች ስራዎችን ለማሻሻል ለአዳዲስ ፈጠራ በቂ ጊዜና ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል

**መምራት** – የተቋሙ አመራሮች ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃዎች ላይ ተመርኩዘው ውሳኔዎችን በፍጥነት በመስጠት ተቋሙን ለመምራት ያስችላል።

**ማስቻል** - ሠራተኞ ትክክለኛውን መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርተው ውሳኔ እንዲሰጡ ያስችላል

# ERP ሲስተም ትግበራ ለኢንፎርሜሽን ኮሙንኬሽን ዳይሬክቶሬት ቀዳሚ ስራው መሆኑ ተገለጸ




የኢንፎርሜሽን ኮሙንኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሀይለሚካኤል ገ/አምላክ የ ERP ሲስተም ትግበራ ስኬታማ እንዲሆን ክፍሉ ትልቅ ሚና እንዳለው ጠቅሰው የዳይሬክቶሬቱ ቀዳሚ ስራ መሆኑን ጥቅምት 02 እና 03 2016 ዓ.ም የ ERP የለውጥ ቡድን ባዘጋጀው በተካሄደው ወርክሾፕ ገልጸዋል፡፡

ዳይሬክተሩ ለሲስተም ትግበራ ስኬታማነት እና ለቀጣይ ሀላፊነትን በአግባቡ ለመዘጋጀት እና በቂ አቅም ይዞ ትግበራውን ለማስቀጠል ክፍሉ ትልቅ ሀላፊነት እንደሚጠብቀው ገልጸው ለዚሁ ዝግጁ ሆኖ መገኘት ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ተግባር መሆኑ ለሰራኞቹ መልዕክት አስተላፈዋል፡፡

ከዚህ በፊት በውስጥ አቅም እና ከውጭ ባሉ የልማት ድርጅቶች አማካኝነት ስራ ላይ ያዋሉ የተበጣጠሱ ሶፍትዌሮች በማዘጋጀት የስራ ክፍሉ የተቋሙ አቅም በመሆን እያገለገለ እንደሚገኙ ገልጸው ይህ አንድ ወጥ የሆነ በአንድ ሲስተም ብቻ የታገዘ የተቀናጀ የመረጃ ስርዓት ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ባለሙያዎች መልካም አጋጣሚ ነው፡፡

ይህ ወርክሾፕ የፕሮጀክቱ የለውጥ አስተዳደር ቡድን ሰራተኞውን ለትግበራ ዝግጁ ለማድረግ ከሚሰራቸው ተግባራት አንዱ ሲሆን የኢንፎርሜሽን ኮሙንኬሽን ባለሙያዎችን ለፕሮጀክቱ ስኬታማነት ትልቅ ሚና ያላቸው በመሆኑ በቀጣይ በሚኖራቸው ሚና ዙሪያ ግልጽነት በመፍጠር ለትግበራው ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ ያለመ ነው፡፡

# የሲስተም ፍተሻ (Testing) ስራው 61% መጠናቀቁ ተገለጸ




የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት የ SAP ERP ትግበራ በሚፈለገው መልኩ መስራቱን ለማረጋገጥ እየተሰራ ያለውን የሲስተም ፍተሻ (Testing) ስራ እስከ ጥቅምት 27 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ 61 % መጠናቀቁን የአማካሪ ድርጅቱ ሲስተም ፍተሻ ማኔጀር አቶ ዳንኤል ደስታ ገለጸ፡፡

ፍተሻው እየተካሄደ ያለው በ11 ሞጁሎች ማለትም Pl2Pr, P2P, S2S, EWM, H2R, In2Rep, TM, O2C, EHS, F2R, እና I2R ላይ ሲሆን በየሞጁሉ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍል የ TOT ስልጠና የወሰዱ 89 ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

ሁሉንም ሞጁሎች ለመፈተሽ የተያዘለት ጊዜ ሁለት ወራት ሲሆን በድምሩ ለሙከራ በተዘጋጁ 939 የመሞከሪያ ናሙና ጽሁፎች (Test script) መሰረት ከመስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ፍተሻ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

ፍተሻው የሲስተም ፍተሻ ሂደቱን ተከትሎ እየተከናወነ ሲሆን በፍተሻ ያላለፉ የመሞከሪያ ናሙና ጽሁፎች በሲዶር በኩል ከተስተካከሉ በኋላ በድጋሚ ፍተሻ ይደረጋል፡፡ ፍተሻው እስከ ህዳር 21 የሚቀጥል መሆኑ በእቅዱ ተመላክቷል፡፡

## ፕሮጀክቱ ለሲስተም ተጠቃሚ ሰራተኞች ስልጠና ለመስጠት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በማከናወን ላይ ነው




የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት የ SAP ERP ትግበራ ፕሮጀክት ስማይል ለሲስተም ተጠቃሚ ሰራተኞች ስልጠና ለመስጠት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በማከናወን ላይ ነው፡፡

ከህዳር 26 ቀን ጀምሮ ለአንድ ወር ያህል ለሲስተም ተጠቃሚ ሰራተኞች ስልጠናው እንደሚሰጥ በእቅዱ የተመላከተ ሲሆን ስልጠናው እንዴት እና በምን ሁኔታ እና ለማን መሰጠት እንዳለበት የመለየት ስራ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በተለያዩ ሞጁሎች የአሰልጣኞች ስልጠና ወስደው የፍተሻ ስራውን በአግባቡ ያከናወኑ ባለሙያዎች ዋና አሰልጣኝ በመሆን እና የ TOT ስልጠና ብቻ የወሰዱ ደግሞ ረዳት አሰልጣኝ በመሆን ስልጣናውን እንደሚያከናውኑ ይታመናል፡፡

# የሲስተም ፍተሻ ስራውን እያከናወኑ የሚገኙ ባለሙያዎች ሰራተኞችን ለማሰልጠን በቂ እውቀት እንዲኖራቸው አግዟዋል




የሲስተም ፍተሻ ስራውን እያከናወኑ የሚገኙ ባለሙያዎች ሰፋ ያለ የልምምድ ጊዜ በማግኘታቸው በሲስተሙ ዙሪያ በቂ እውቀት እንዲያገኙ እንዳገዛቸው ባለሙያዎቹ ገለጹ፡፡


የፕሮጀክት ሰራተኞችን ጨምሮ ከዋና መስሪያቤት እና ከቅርንጫፍ የተወጣጡ ባለሙያዎች የ TOT ስልጠና በወሰዱበት ወቅት የጠለቀ እውቀት እንዳልነበራቸው ገልጸው የፍተሻ ስራውን በመስራታቸው በሲስተሙ ዙሪያ ያላቸውን እውቀት እንዲጨምር አድርጎታል ብለዋል፡፡

አንዳንድ የፍተሻ ስራውን የሚያከናውኑ ባለሙያዎች እንደገለጹት በቀጣይ ለሚሰጠው ሰራተኞችን የማሰልጠን ስምሪት በብቃት ለመወጣት ምቹ ሁኔታ የፈጠረ መሆኑን አክለው ገልጸዋል፡፡

በየሞጁሉ ከመስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እየተከናወነ ያለውን የሲስተም ፍተሻ ስራ ሲስተሙ አገልግሎቱ በሚፈለገው መልኩ መስራቱን ፍተሻውን የሚያከናውኑ ባለሙያዎች በፊርማቸው ካረጋገጡ በኋላ ሰራኞችን የሚያሰለጥኑ ይሆናል፡፡


ፕሮጀ]ክቱ የሶስተኛ ምዕራፍ ተግባራትን አጠናቆ የአራተኛ ምዕራፍ ተግባራትን በማከናወን ላይ ሲሆን በየሞጁሎች በተዘጋጁ የናሙና ጽሁፎች (TEST SCRIPT) መሰረት የሲስተም ፍተሻ ስራውን እያከናወነ ይገኛል፡፡

## SAP S/4HANA SYSTEM TESTING IS ONGOING



ፕሮጀክቱ የሲስተም ፍተሻ ስራውን አከናውኖ ካጠናቀቀ በኋላ የሲስተም ተጠቃሚ ሰራተኞች የሚሰለጥኑ ይሆናል፡፡ለዚህም የቅድመ ዝግጂት ስራዎች በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

## After Completing the Testing program the project moved to staff training



## በ ERP ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚደረጉ ሞጁሎች የምህጻረ ቃል ጥርጉም

| | |
|---|---|
| Pl2Pr | Plan to Procure |
| P2P | Procure to Pay |
| S2S | Store to Ship |
| EWM | Embedded Extended warehouse |
| In2Rep | Inspect to Repair |
| F2R | Record to Report |
| H2R | Hire to Retire |
| O2C | Order to Cash |
| TM | Transport Management |
| I2R | Inspect to Release |
| EHS | Environmental Health & safety |